BAJI
BLACK ALLIANCE FOR JUST IMMIGRATION

# የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት እቅድ

## መብትዎን ይወቁ

ማንኛዉም በአሜሪካ ውስጥ የሚኖር ሰዉ ሰነድ ይኑረዉም አይኑረውም መብት አለው።

ያለ ምንም ህጋዊ የመያዣ ትእዛዝ ለአይስ ወይም ለማንኛውም የፖሊስ ኦፊሰር የቤትወን በር አይክፈቱ ።

ከአይስ ጋር መነጋገር ወይም ለጥያቄዎቻቸው መልስ መስጠት አያስፈልግዎትም። ዝም የማለት መብት አለዎት እናም ለአይስ ጥያቄዎች መልስ አለመስጠት ይችላሉ። ከጠበቃዎ ጋር እስኪነጋገሩ ድረስ ዝም ማለት እንደሚትፈልጉ ይንገሩአቸው።

ለማንኛውም አይነት ጥያቄ መልስ አይስጡ፤ በተለይም የትውልድ ቦታዎትን፣ የኢሚግሬሽን ስታተስዎን/ወረቀትዎን ወይም ወደ አሜሪካ የገቡበትን መንገድ በተመለከተ መልስ አይሰጡ።

ስለ ራስዎም ሆነ የቤተሰብዎ አካል ስለሆነ ማንኛውም ሰው የግል መረጃን ለአይስ አይስጡ ።

ልጆችዎትን እና ሌሎች የቤተሰብዎን አባላት ጋር በመሆን ለአይስ "አይሆንም" እንዲሉ ያለማምዱ።
ለፍተሻ ፍቃደኛ ያለመሆን መብት አለዎት።

**ቤተሰብዎ የሆነን ሰው ከአይስ ማረሚያ ቤት ውስጥ ለማግኘት፡**
ዘመድዎን ከአይስ የእስር ቤት ለማግኘት በአይስ ድረ ገጽ ላይ "Online Detainee Locator System" (ODLS) ይጠቀሙ። በዚህ ድረ-ገጽ ላይ በሙሉ ስማቸው፣ በትውልድ አገራቸው፣በተወለዱበት ቀን ወይም በA-Number (የዉጭ ሀገር ዜጋ የምዝገባ ቁጥር/ alien registration number) መፈለግ ይችላሉ።
አብዛኛውን ጊዜ መረጃዎቻቸውን በሚከተለው ሊንክ በ48 ሰዓታት ውስጥ ማግኘት ይቻላል ፡-
https://locator.ice.gov/odls/#/search
በአይስ እስር ቤት ውስጥ ላለ ዘመድዎት መደውል ይችላሉ፤ ሆኖም ስልክ ለመደወል የሚያስችለውን አሠራር ለማወቅ የሚመለከተውን አካል ማነጋገር ያስፈልግዎታል፤ ይህ ደግሞ ስልክ ለማውራት የጊዜ ገደብ አና ከታሰሩት ሰዎች መካከል ስልክ እንዲደወልላቸው አነማን አንደሆኑ ገደብ ሊኖረው ይችላል።

## ለቤተሰብ ዝግጅት እቅድ ጠቃሚ ምክሮች:

- **ሁሉም ቤተሰቦች፣** የኢሚግሬሽን ስታተስዎ/ወረቀትዎ ምንም ይሁን ምን፣ **ላልተጠበቁ ድንገተኛ አደጋዎች ሊዘጋጁ ይገባል።**
- እምነት የሚጥሉበት የህጻናት ጠባቂ እቅድ ይኑርዎት፣ምክንያቱም ልጅዎን መያዝ በማይችሉበት ወቅት ለጅዎትን ለእነሱ መሰጠት ይችላሉ።
- ልጅዎትን እንዲንከባከብ የመደቡት ሰው የአሜሪካ ዜጋ ወይም የኢሚግሬሽን ወረቅት ያለው እና የመታሰር ወይም ከአገር የመባረር ሥጋት የማያጋጥመው ሰው መሆን አለበት።
- ይህ ሰው እንደ አስቸኳይ ጊዜ ተጠሪ እንደሚዘረዘር እና ሁሉንም አስፈላጊ ሰነዶችዎን እና መረጃዎን እንዴት ማግኘት እንደሚችል እንደሚያውቅ እርግጠኛ ይሁኑ.
- ልጆችዎን ከቦታዉ ማመላለስ የሚችሉ እና የማይችሉትን ስም ለማካተት የአስቸኳይ ጊዜ አገናኝ ገጾችን እና መልቀቂያ ቅጾችን ያሻሽሉ።
- ልጅዎ ማንኛውም አይነት የጤና ችግር ካለበት እና /ወይም ማንኛውንም መድሃኒት የሚወስድ ከሆነ መመሪያዎችን ይፃፉ። ለሚንከባከባቸው ሰው፣ለእራስዎ፤ እንዲሁም ለልጃችሁ ትምህርት ቤት አንድ ኮፒ/ቅጂ ይስጡ/ይያዙ።

## በአይስ ከልጆችዎት ጋር ተለያይተው ከሆነ...

- ልጅ እንዳልዎት ለኦፊሰሮች በመናገር ወላጅነትዎን ያረጋግጡ፣ ለልጆችዎ እንክብካቤ ለማመቻቸት ስልክ መደወል እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው፣ በዚህም ወደ እስር ቤት እንዳይገቡ ይሆናሉ።
  - ለልጆችዎ አስቀድመው ተንከባካቢ ያዘጋጁ፤ እንዲሁም በሕዝብ መዝጋቢ ፊት የፋይናንስ ኃይል ፎርም ይፈርሙ።

የባጂ የድጋፍ ወርክሾፕ!
የባር ኮዱን ስካን በማድረግ ወይም ይሄንን ዌብሳይት በመጫን ይቀላቀሉን https://bit.ly/BAJILegalClinics.
ለቀን እና ለሰአት በዚህ እሜል ወይም ስልክ ያግኙን: legal@baji.org እና +1 516-967-3238
(ስልክ/መልክት/ዋትሳፕ)